የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ መስከረም ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.39
ADDIS ABABA 15th September, 2023

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፯/፪ሺ፲፭
የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (ማሻሻያ) ገፅ..........፲፭ሺ፩፻፮

**Content**

Proclamation No. 1287/2023
Excise Tax (Amendment) Proclamation..........Page 15106

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፯/፪ሺ፲፭**

**የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

ወደአገር በሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎች እና አንዳንድ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን እጅግ በጣም ከፍተኛ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ጭምር ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው እንዲያስገቡ መፍቀድ ተገቢ ባለመሆኑ፤

የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልበት ማድረግ መንግሥት ለሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች የሚውል ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ስለታመነበት፤

**PROCLAMATION NO. 1287/2023**

**EXCISE TAX (AMENDMENT) PROCLAMATION**

**WHEREAS**, it has become necessary to lower the exaggerated excise tax rate imposed on imported new vehicles and some other items;

**WHEREAS**, it is found not proper to grant persons and organizations with special tax and duty privileges to also import goods on which excise tax is imposed because of the damage they inflict on the environment free of excise tax;

**WHEREAS,** it is believed that imposing excise tax on telecommunication services will help generate more revenue to finance development activities carried out by the Government;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ (ማሻሻያ) ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፯/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ማሻሻያ

የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፮/፪ሺ፲፪ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡-

፩/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፪) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፫)፤ (፳፬) እና (፳፭) ተጨምረው በነባሩ ከንዑስ አንቀጽ (፳፫)-(፴፬) የሆኑት እንደቅደም ተከተላቸው ከንዑስ አንቀጽ (፳፮-(፴፯) ተደርገው ተሸጋሽገዋል፡-

"፳፫/ "ኤቲይል አልኮል" ማለት ጥራቱ ፹ ዲግሪ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ አልኮል ነው፤"

"፳፬. "አዲስ ተሽከርካሪ" ማለት ከተመረተበት ዓመት ጀምሮ ከዚህ በታች ከተመለከተው በላይ አገልግሎት ያልሰጠ ተሽከርካሪ ሲሆን፤ የሚከተሉትን ይጨምራል:-

ሀ) በሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ እንዲገጣጠም ሙሉ በሙሉ ተበትኖ ወደአገር የገባ ወይም በከፊል ተበትኖ ወደአገር የገባ ተሽከርካሪ፣

ለ) በጉምሩክ ታሪፍ በአንቀጽ ፹፯ ነጥብ ዜሮ፪፣ ፹፯ ነጥብ ዜሮ፫፣ ፹፯ ነጥብ ዜሮ፬፣ ፹፯ ነጥብ ዜሮ፭ እና ፹፯ ነጥብ ፲፩ የሚመደብ ሆኖ፤ ሙሉ በሙሉ ተገጣጥሞ ወደአገር የገባ፤ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) በደረሰበት ጊዜ የተመረተበትን የዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ዕድሜው ከሶስት ዓመት የማያልፍ እና ከውጭ አገር እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) ድረስ የተነዳው ርቀት ከ ፬ሺ ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፣

**NOW THERFORE**, in accordance with Article 55(1) and Article (11) of Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows.

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Excise Tax (Amendment) Proclamation No. 12872022".

## 2. Amendment

The Excise Tax Proclamation No. 1186/2020 (as amended) is hereby further amended as follows:

**1**/ The following new Sub-Articles (23), (24) and (25) are added after Sub-Article (22) of Article 2 and the existing Sub-Articles (23)-(34) are renumbered from (26)-(37) respectively:

"**23/ "Ethyl Alcohol**" means alcohol of purity of 80 degrees or more;"

"**24/ "New Vehicle**" means a vehicle that has not been used over what is stated in this Sub-Article since its manufacturing year and includes the following:

a) imported in semi-knocked Down (SKD) or Complete Knocked Down (CKD) form to be assembled by local industry ,

b) a Complete Built Up (CBU) vehicle of tariff heading 87.02, 87.03, 87.04, 87.05 and 87.11 which arrives at the Ethiopian customs territory (entry point) within a time period of three Gregorian calendar years including the manufacturing calendar year of the vehicle and when the number of kilometers driven abroad at the time it arrives at the Ethiopian custom territory (entry point) does not exceed 4,000 kilometers,

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ "ለ" በታሪፍ አንቀጽ ተለይተው ከተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች ውጪ በሚሆንበት ጊዜ ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ በሚቆጠር በአራት የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ውስጥ በኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰ ነው፡፡"

"፳፭/ "ያገለገለ ተሽከርካሪ" ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፳፬) ለአዲስ ተሽከርካሪ በተሰጠው ትርጉም የማይሸፈን ተሽከርካሪ ሲሆን፣ የአገልግሎት ዘመኑም ተሽከርካሪው የተመረተበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ጨምሮ እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል (መግቢያ በር) የደረሰበትን የጎርጎሮሳውያን ዘመን መቁጠሪያ ዓመት ይጨምራል፡፡"

፪. የአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል:-

"፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ በተደነገገው መሰረት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፩ የተዘረዘሩት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በሰንጠረዡ በተመለከተው የማስከፈያ ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡"

፫. የአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡፡

"፫/ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፩ በተመለከተው በጉሙሩክ ታሪፍ ምዕራፍ፲፭ በሚመደበው የእንስሳት ወይም የአትክልት ስብና ዘይት እና የእነዚህ ተዋፅዖ ውጤቶች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ መሰብሰብ የሚጀመርበትን ቀን ከጤና ሚኒስቴር በሚደርሰው መረጃ መሰረት በገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

c) if the vehicle is not covered under Pharagraph (b) of this Sub-Article it arrives at Ethiopian custom territory (entry point) within a time period of four Gregorian calendar years including the manufacturing calendar year of the vehicle."

"25/ "**Used Vehicle**" means a vehicle not covered under Sub-Article (24) of this Article and the age is counted beginning the manufacturing Gregorian calendar year to the Gregorian calendar year of its arrival at Ethiopian customs territory (entry point)."

2. Sub-Article (2) Article 5 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2/ Excise Tax shall be charged at the rate specified in the first Schedule attached herewith for the excisable goods and services in force at the time the liability arises for Excise Tax as determined under Article 9 of this Proclamation."

3. A New Sub-Article (3) has been added after Sub-Article (2) of Article 5 of the Proclamation.

"3/ The commencement date for collection of excise tax charged on edible animal or vegetable fats and oils and their cleavage products specified in Schedule 1 attached herewith as classified in Chapter 15 of the Customs Tariff shall be determined by the Ministry of Finance based on the information it receives from the Ministry of Health."

፬. የአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ ፩ ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው ተራ ፊደል (ሀ) ተተክቷል፡

“፩. ሀ) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ፪ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤”

፭. ከአዋጁ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፤

“፭/ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት የባንክ ፈቃድ አግኝተው ከማናቸውም ቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ዕቃዎች ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወደአገር የሚገቡ ከሆነ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ አይደረጉባቸውም፡፡”

## ፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሚያዚያ ፳፩ ቀን ፳፻፲፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም ፭ ቀን ፳፻፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ-ወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

4. Sub-Article 1 Pharagraph (a) of Article 8 is deleted and replaced by the following new Pharagraph (a)’:

“1/ a) exempt goods which meet the conditions set out under the Second Schedule attached with this Proclamation;”

5. The following new Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) of Article 43;

“5/ This Proclamation shall not be applicable for Excise Tax on goods to be imported into Ethiopia free of any taxes and duties, for which bank permit has been obtained prior to the enactment of this Proclamation and imported within two months from the effective date of this Proclamation.”

## 3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its adoption by the House of Peoples Representatives on the 29 day of April 2023.

**Done at Addis Ababa, On this 15th Day of September, 2023**

**SAHLE-WORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**